# <u>መመሪያ ቁጥር 30/2013</u>

# <u>የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ</u>

የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና የሚያስከትለው ጉዳት ለመቀነስ ስለ ሚወሰዱ ክልከላዎች እና ግዴታዎች በህግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በመድኃኒትና ምግብ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 72 ንዑስ-አንቀፅ (2)፣ በምግብ፣መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661 አንቀፅ 55 ንዑስ-አንቀፅ (3) እና የምግብ፣ የመደኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀፅ 98 መሰረት የሚከተለውን መመሪያአውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1. <u>አጭር ርእስ</u>**

ይህ መመሪያ "**የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁጥር 30/2013**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**2. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

**Directive No 30/2020**

# A DIRECTIVE ISSUED FOR THE PREVENTION AND CONTROL OF COVID-19 PANDEMIC

WHEREAS, it has become necessary to provide the particulars of prohibited activities and duties to be imposed on individuals to prevent and mitigate the impact of COVID-19

NOW, THEREFORE, this Directive is issued by the Ethiopian Public Health Institute in accordance with Article 72 (2) of the Food and Medicine Administration Proclamation No. 1112/2019, Article 55(3) of the Food, Medicine, and Healthcare Administration and Control Proclamation No. 661/2009, and Article 98 of the Council of Ministers Regulation on Food, Medicine, and Healthcare Administration and Control No. 299/2013.

## Part One

## General

**1. Short Title**

This Directive may be cited as "A Directive issued for the Prevention and Control of the COVID-19 Pandemic" No. 30/2020".

**2. Definition**

In this Directive, unless the context requires otherwise:

1. "ኮቪድ-19" ማለት በአለም የጤና ድርጅት በይፋ በዚህ ስም የሚጠራው ተላላፊ በሽታ ነው፣
2. ‘’አካላዊ መራራቅ’’ ማለት የኮቪድ-19 በሽታከሰው ወደ ሰው የሚኖረውን ስርጭት ለመቀነስ ወይንም ለመግታት በሁለት ወይንም ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ወይንም ሁለት ሜትር እና ከዛ በላይ ርቀትን መጠበቅ ነው፣
3. ‘’ስብሰባ’’ ማለት ማንኛውንም ተግባር ለመፈጸም፣ ለመነጋገር፣ስልጠና ለመስጠት፣ ለመወያየት፣ ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣ ወይም መሰል ተግባራትን ለማከናወን የአንድ ቤተሰብ አባላት ከሆኑ ውጪ አራትና ከዚያ በላይ ሆኖ በአንድ ቦታ በአካል መገኘት ነው፣
4. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የጤና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
5. "ዲፕሎማት" ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ደረጃ አላቸው ተብሎ የተረጋገጠላቸው ሰዎች ማለት ነወ፤

1. “COVID-19” means the communicable disease designated as such by the World Health Organization
2. “physical distancing” means the practice of keeping at least two adult strides or two-meter apart between two or more people to reduce or halt the human to human transmission of COVID-19;
3. “Meeting” means the gathering of four or more persons who do not belong to a single family, in one place for the purpose of collectively carrying out any activity, discussion, or any similar purposes;
4. “Ministry or Minister” means the Ministry of Minister of Health respectively;
5. “Diplomat” mean those persons recognized by the Ministry of foreign affairs as having diplomatic status.

6. "የቤት ውስጥ መቆያ" ማለት መኖሪያ ቤት ሆኖ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር በሚያስችል መልኩ መስኮት ወይም አየር ማስገቢያ ያለው እና ለኮቪድ 19 በሽታ የተጋለጡ፣ የተጠረጠሩ ወይንም ተመርምረው በበሽታው መያዛቸው የተረጋገጡ ሰዎች የሚቆዩበት ስፍራነው፣
7. "ከስደት ተመላሽ" ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ከኢትዮጵያ ወጥቶ በስደት የኖረና በራሱ ፈቃድ ወይንም በመንግስት ስምምነት ያለ ፓስፖርት ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ወይም በተቀባዩ አገር የጥገኝነት ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ እና በራሱ ፈቃድ በሊሴ ፓሴ ወይም በነበረበት አገር መንግስት ተገዶ ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ነው፣
8. "ሞት" ማለት በጤና ተቋም ወይም ከጤና ተቋም ውጭ በማንኛውም ምክንያት የሚከሰት ሞት ነው፣
9. "ቀላል የኮቪድ-19 ታካሚ" ማለት በኮቪድ-19 የተያዘ ሆኖ የሳንባ ምች በሽታን ወይም ሌሎች የኮቪድ-19 ከፍተኛ ህመም ምልክቶችን የማያሳይ ታካሚ ነው፣
10. "ምልክት የሌለው የኮቪድ-19 ታካሚ" ማለት ምንም አይነት የበሽታውን ምልክቶች የማያሳይ በኮቪድ-19 የተያዘ ሰው ነው፣

6. "home isolation" means a residential house equipped with an operable window and door to allow adequate air ventilation of air and used by people exposed, suspected of, or confirmed to have contracted COVID-19 isolate themselves;
7. "returnee" means any Ethiopian who left Ethiopia for a different reason as a refugee and is in the process of returning to the territory of Ethiopia on his own or per government agreement without a passport, or any Ethiopian whose asylum petition is denied by the receiving country and is in the process of returning to the territory of Ethiopia on his own wish or compelled to be deported by the government of his temporary residence with a Laissez-passer;
8. "death" means the end of life caused by any reason and that occurred within or outside of health institutions;
9. "mild COVID-19 patient" means any person with conformed COVID-19 and have no manifestation of pneumonia or other severe symptoms of COVID-19;
10. "asymptomatic COVID-19 patient" means any person with conformed COVID-19 who does not develop any manifestation of pneumonia or other severe symptoms of COVID-19;

11. "የኮቪድ-19 ምልክቶች" ማለት በኮቪድ-19 የተያዘ ሰው ላይ ሊስተዋሉ የሚችሉ እንደ ትኩሳት፣ የራስ ምታት፣ የሳል፣ ጣዕምና ሽታን መለየት አለመቻል፣ የጉሮሮ አካባቢ ቁስለቶችና የመሳሰሉ ምልክቶች ናቸው፣

12. "RT PCR" ማለት በሞለኪዉላር ቴክኒክ የኮሮና ቫይረስ ምርመራ ስርዓት ነው፣

13. "RDT" ማለት ፈጣን የ ኮቪድ 19 የምርመራ አይነት ነው፣

14. "ኮቪድ 19 ፖዘቲቭ" ማለት በRT PCR ወይም ሌሎች ቫይረሱ በሰውነት ውስጥ መኖሩን ሊያሳዩ በሚችሉ የምርመራ አይነቶች ቫይረሱ የተገኘበት ሰው ማለት ነው፣

15. "ኮቪድ 19 ኔጌቲቭ" ማለት በRT PCR ወይም ሌሎች ቫይረሱን በሰውነት ውስጥ መኖሩን ሊያሳዩ በሚችሉ የምርመራ አይነቶች ቫይረሱ ያልተገኘበት ሰው ማለት ነው፣

16. "ጸረ ተህዋሲያን ውህድ" ማለት ከኮሮና ቫይረስ ጋር ንክኪ ይኖርቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ እቃዎች ለማጽዳት የሚውል ከአልኮል ወይም ክሎሪን የተዘጋጀ ውህድ ማለት ነው፣

11. "COVID-19 symptoms" means any symptoms manifested by a person with COVID-19 including fever, headache, cough, loss of taste and smell, throat swelling, and similar other symptoms;

12. "RT PCR" means a laboratory diagnosis of COVID-19 through molecular techniques;

13. "RDT" refers to a Rapid Diagnostic Test for COVID-19 which is an accelerated laboratory diagnosis procedure;

14. "COVID-19 positive "means any person whose COVID-19 infection is confirmed through RT PCR, or other similar other laboratory diagnosis method to detect the presence of the virus in the human body ;

15. "COVID-19 negative "means any person the absence of his COVID-19 infection is confirmed through RT PCR, or other similar other laboratory diagnosis method to detect the presence of the virus in the human body;

16. "disinfectants" means alcohol or chlorine-based compound and intended to disinfect articles or materials supposed to harbor COVID-19;

17. “ክልል’’ ማለት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 47 የተመለከተ ወይም የተመሰረተ ማንኛዉም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደሮችም ይጨምራል፤

18. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው፣

19. “ቤተሰብ” ማለት በአንድ ቤት ውስጥ በአንድ ላይ የሚኖሩትን አባላት ማለት ነው፣

20. በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴትንም ፆታ ያካትታል፣

**3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል::

## ክፍል ሁለት

## የተከለከሉ ተግባራት እና የተጣሉ ግዴታዎች

**4. የተከለከሉ ተግባራት**

1. ማንኛውም ኮቪድ-19 ያለበት ሰው ቫይረሱ እንዳለበት እያወቀ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት፣ ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል ወይም ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ በሚችልበት ሁኔታ ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘት የተከለከለ ነው፣

17. “region” means the states established in accordance with Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the administration of the Addis Ababa and Dire Dawa cities;

18. “person” includes any natural and legal person;

19. “family” means household members who live in a house; and

20. any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. Scope of application**

The Directive shall be applicable to all efforts to be done in Ethiopia to prevent and control the COVID-19 pandemic.

## Part Two

## Prohibited Activities and Duties Imposed

**4. Prohibited Activities**

1. It is prohibited for any person who knows he infected with COVID-19 to enter the country, mix with the general public or meet with people in any situation that may allow the virus to spread;

2. ማንኛውም ሰው ለሰላምታና ሌላ ለማንኛውም አላማ በእጅ መጨባበጥ፣ሆነ ብሎ የእርስ በእርስ አካላዊ ንክኪ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
3. ማንኛውም ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ ቀሪ መሆኑ እስከሚወሰንበት ጊዜ ድረስ ከመኖርያ ቤት ውጪ በማንኛውም በታ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርግ መገኘት ወይም መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው፣ ሆኖም ዕድሜያቸው ከስድስት አመት በታች የሆነ ህጻናት ወይም በማስረጃ የተረጋገጠ የመተንፈሻ አካላት ወይም መሰል ችግር ያለባቸው ሰዎች ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንባቸውም፣
4. በማንኛውም መንግስታዊ እና ግል ተቋም ሰራተኞች ከሁለት የአዋቂ እርምጃ በታች ተጠጋግተው እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርጉ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣ ተገልጋዮች በሚቀመጡበት ጊዜም ይሁን በማንኛዉም አኳኋን አገልግሎቱ ሲያገኙ ከሁለት የአዋቂ እርምጃ በታች ተጠጋግተው እና የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርጉ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ወይም በአንድ ጠረጴዛ ከሶስት ተገልጋዮች በላይ እንዲቀመጡ ማድረግ የተከለከለ ነው፣

2. It is prohibited for any person to shake hands with another as a greeting or for any other purpose; it is prohibited to make deliberate physical contact with each other;
3. Until it is decided wearing a mask is no longer necessary, it is prohibited for any person to be found without a mask anywhere outside his residence or move from one place to another. Nevertheless, this provision is not applicable to minors who are under 6 years of age or individuals having the respiratory or other related medical case that can be proven by evidence.
4. It is prohibited for employees of any public or private organization to provide service without maintaining a distance of two adult strides and without wearing masks; it is prohibited to provide service to individuals who are not maintaining a distance of two adult strides and not wearing masks or to serve more than three patrons at a single table;

5. ማንኛውም የንግድ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ ቀሪ መሆኑ ካልተወሰነ በስተቀር አፍና አፍንጫውን ላልሸፈነ ሰው አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፣

6. በክፍት ገበያዎች፣ በትራንስፖርት መሰፈሪያ በታዎች፣ ህዝባዊ አገልግሎት በሚሰጥባቸው በታዎችና ሌሎች ህዝብ በሚበዛባቸው መሰል አካባቢዎች ከሁለት የአዋቂ እርምጃ በታች ርቀት መቆምም ሆነ መቀመጥ የተከለከለ ነው፣ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ አለም አቀፍ ኤርፖርቶችን በተመለከተ አለም አቀፍ ሲቪልአቪየሽን ድርጅት፤ አለምአቀፍ የአየር መንገዶች ማህበር እንዲሁም የአለም ኤርፖርት ድርጅት የሚያወጦቸውን መሰፈርቶች ባገናዘበ መልኩ በዘርፉ በሚወጡ መመሪያዎች የሚከናወን ይሆናል፣

7. ማንኛውም የግልም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤት የፊትለፊት ትምህርት መስጠት መጀመር እንደሚቻል ሳይወሰን እንዲሁም ትምህርት የሚሰጥበትን ሁኔታ ወይም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስራውን በተመለከተ በመመሪያ የሚወጡ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር ወይም ሌሎች ዝርዝር የትምህርት አሰጣጥ

5. Until it is decided wearing a mask is no longer necessary, it is prohibited for any business organization to provide service to any person who is not covering his mouth and nose;

6. It is prohibited to stand or sit without maintaining a distance of two adult strides in market places, transport depots, places where public services are provided or any other public space where a large number of people are found; Without prejudice to the preceding statement, the case of all international airport in Ethiopia shall be handled by a special directive issued by the respective sectors having regard to criteria set by International air ports, International aviation and international air lines association.

7. It is prohibited for any public or private school to provide education until it is decided it is possible to conduct classes face-to-face or without respecting the directives that shall be enacted regarding precautionary measures in methods of education delivery or the general teaching and learning work or other detailed standards of education delivery;

ስታንዳርዶችን ሳይከተል ትምህርት መስጠት የተከለከለ ነው፣

8. ማንኛውም የግልም ሆነ የመንግስት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የፊትለፊት ትምህርት መስጠት መጀመር እንደሚቻል ሳይወሰን እንዲሁም የሚሰጥበትን ሁኔታ ወይም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስራውን በተመለከተበመመሪያ የሚወጡ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር ወይም ሌሎች ዝርዝር የትምህርት አሰጣጥ ስታንዳርዶችን ሳይከተልትምህርት መስጠት የተከለከለ ነው፣

8. It is prohibited for any public or private college or university to provide education until it is decided it is possible to conduct classes face-to-face or without respecting the directives that shall be enacted regarding precautionary measures in methods of education delivery or the general teaching and learning work or other detailed standards of education delivery;

9. ማንኛውም የህጻናት ማቆያ ማዕከል አገልግሎት መስጠት እንደሚቻል ሳይወሰን እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ በተመለከተ በመመሪያ የሚወጡ ሊወሰዱ የሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያከብር አገልግሎት መስጠት አይችልም።

9. It is prohibited for any daycare center to provide service until it is decided it is allowed to provide service and without respecting the directives that shall be enacted on the manner of providing the service taking precautionary measures.

## 5. የተጣሉ ግዴታዎች

## 5. Duties Imposed

1. ማንኛውም ኮቪድ 19 በሽታአለብኝ ብሎ እራሱን የሚጠረጥር ሰው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት በማድረግ የመመርመርና ቫይረሱ ወደ ሌሎች እንዳይተላፍ አስፈላጊውንጥንቃቄ የማድረግ ሀላፊነት አለበት፣

1. Any person who suspects he is infected with COVID-19 has a duty to be tested by reporting to the appropriate body and shall take the necessary precautionary measures to prevent the virus from being transmitted to others;

2. በሽታው አለበት ተብሎ የሚጠረጠር ሰው ሰለመኖሩ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ለጤና ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣በአቅራቢያው ለሚገኙ የጤና ተቋም ወይም ባለሞያ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

3. ማንኛውም አገልግሎት የሚሰጥ የመንግስታዊ እና የግል ተቋም አገልግሎቱን ለማግኘት ወደ ተቋሙ ለሚመጡ ተገልጋዮች በዚህ መመሪያ ወይም የሚመለከተው ዘርፍ በመመሪያ በሚያወጣው የጥንቃቄ እርምጃ መሰረት ቫይረሱን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳሶችን የማቅረብ፣ ተገልጋዮች ሁለት የአዋቂ እርምጃ ተራርቀው የሚቆሙበትን ቦታ ምልክት የማድረግ እና ተገልጋዮች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን እና ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎችንመተግበራቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፣

4. ማንኛውም የመንግስታዊ እና የግል ተቋማት ለሰራተኞች ስለበሽታው አስፈላጊውን መረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማድረስ፣ በመግቢያና መውጫ በሮችና ሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን የማዘጋጀት ፣ የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ

2. Any person shall inform the Ministry of Health, the Ethiopian Public Health Institute, the nearest health institution, or official of any person he suspects of being infected with the disease.

3. In accordance with this Directive or any other directive on precautionary measures enacted by the appropriate sector, any public or private service provider shall provide sanitary materials useful for preventing the spread of the virus, mark spots where customers could stand maintaining a two adult stride distance, ensure that customers are wearing masks and taking the necessary precautionary measures;

4. Any public or private organization shall use various mediums to make information regarding COVID-19 accessible to their employees; provide materials useful to prevent the disease at their gates and other necessary places; provide precautionary materials useful to prevent the spread of the disease; ensure that they are wearing masks and taking other necessary precautionary measures;

ቁሳቁሶችን የማቅረብ፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን እና ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎችንመተግበራቸውን የማረጋገጥግዴታ አለባቸው፣

5. ማንኛውም የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ሀገር አቀፍም ሆነ የከተማ ውስጥ ትራንስፖርትን በተመለከተ በህግ ከሚወሰነው የመጫን አቅም ልክ ሰዎችን የመጫን፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ያላደረጉ ሰዎችን አገልግሎት አለመስጠት፣ መስኮቶችን በመክፈት በተሽከርካሪው ውስጥ በቂ የአየር ዝውርውር እንዲኖር የማድረግ እና በዘርፉ በመመሪያ የሚወጡ ሌሎች መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች በመተግበር አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፣

5. Any cross country or inter-city transport service providers have a duty to carry passengers in accordance with the law setting the maximum carrying capacity, deny service to individuals who are not wearing masks; open windows to allow sufficient air circulation in the vehicle and provide service by implementing other necessary precautionary measures provided in directives enacted by the sector;

6. የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አሰሪዎች በግንባታ ሳይቶች ላይ አስፈላጊውን ንጽህና ለመጠበቅ የሚረዱ እንደ ውሃ፣ ሳሙና፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ፣ ሳኒታይዘር ወይንም አልኮል፣ የሙቀት መለኪያ መሳሪያ እንዲሁም የጸረ ተህዋሲያን ግብዓት የማቅረብ ወይንም የሟሟላት፣ ሰራተኞች በተቻለ መጠን ርቀታቸው ጠብቀው እንዲሰሩ የማድረግ፣ እንዲሁም በኮንስትራክሽን ዘርፍ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተጋላጭነትን ለመከላከል፣ ዝግጁነት ለማረጋገጥና ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታን

6. Construction project employers have a duty to provide the necessary sanitary materials such as water, soap, mask, sanitizer or alcohol, thermometer and anti-viral materials on the construction sites; ensure the employees work maintaining their distance to the extent possible; respect and make sure others respect precautionary measures provided in directives enacted by the sector to prevent proneness to the COVID-19 pandemic in the construction sector;

በተመለከተ በዘርፉ በመመሪያ የሚወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች የማክበር እና የማስከበር ግዴታዎች አለባቸው፣

7. ማንኛውም በሆቴል፣ በአስጎብኚነት እና በሌሎችም የቱሪዝም መስክ የተሰማሩ ተቋማት በሰራተኞቻቸው እና ተገልጋዮቻቸው መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ወይም የሁለት ሜትር ርቀት እንዲኖር የማድረግ፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን የመቆጣጠር፣ በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን የማዘጋጀት ፣ ለሰራተኞቻቸው የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን የማቅረብ፣ እንዲሁም የቱሪዝም አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ዘርፉ በመመሪያ የሚያስቀምጣቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

8. ማንኛውም በኢንዱስትሪ እና ምርት መስክ የተሰማሩ መንግስታዊ እና የግል ተቋማት ለሰራተኞቻቸውስለበሽታው አስፈላጊውን መረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማድረስ፣ በመግቢያና መውጫ በሮችና ሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን ማዘጋጀት፣ የስራ ቦታዎችን በቂ የአየር ዝውውር ሊኖርበት በሚችል መልኩ

7. Any hotel, tour operator and others organizations in the tourism sector have a duty to make sure there is a distance of two adult strides or two meters between their employees and customers, ensure they are wearing masks, prepare materials necessary to prevent the disease, provide their employees with precautionary materials useful to prevent the spread of the disease, and provide tourism services by taking precautionary measures provided in directives enacted by the sector;

8. Any public and private organizations in the industry and production sector have a duty to use various mediums to make information regarding the disease accessible to their employees; provide materials useful to prevent the disease at their gates and other necessary places; rearrange working places to allow sufficient air circulation; provide precautionary materials useful to prevent the spread of the disease, ensure employees wear masks and

የማደራጀት፣የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን የማቅረብ፣ ሰራተኞች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረጋቸውን እና ሌሎች አስፈላጊ ጥንቃቄዎችንመተግበራቸውን የማረጋገጥ፣ እንዲሁም ሌሎች ዘርፉ በመመሪያ የሚያስቀምጣቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

implement other necessary precautionary measures; and take other precautionary measures provided in directives enacted by the sector;

9. በዚህ አንቀጽ ውስጥ ከተዘረዘሩት ዘርፎች በተጨማሪ በሌሎች ማንኛውም ዘርፍ ላይ ያለ ማናቸውም መንግስታዊም የሆነ የግል ተቋም የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተጋላጭነትን ለመከላከል፣ ዝግጁነት ለማረጋገጥ እና ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታን በተመለከተ በዘርፉ በመመሪያ የሚወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎች የማክበር እና የማስከበር ግዴታ አለበት።

9. In addition to the sectors provided in this article, any public or private organization in other sectors has a duty to respect and make others respect precautionary measures provided in directives enacted by the sector to prevent proneness to the COVID-19 pandemic, ensure preparedness and determine manner of responsiveness.

## ክፍል ሶስት

## በቤት ውስጥ ማቆያ እናክብካቤ ወቅት መደረግ ስላለበት ጥንቃቄ

## Part Three

## Precautionary Measures for Home Isolation and Care

### 6. በቤት ውስጥማቆያእና ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ

በጤና ሚኒስቴር በሚዘጋጀው ማንዋል መሰረት ማንኛውም ቀላል ወይም ምንም አይነት የኮቪድ-19 ምልክት የሌለበት የኮቪድ 19 ታማሚ በቤት ውስጥ የኮቪድ 19 ህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል።

### 6. Providing home isolation and caring service

In accordance with the manual that shall be prepared by the Ministry of Health, any mild COVID-19 patient or asymptomatic COVID-19 patient may receive medical treatment for COVID-19 at home.

7. **በቤት ውስጥማቆያ እና ክብካቤ ላይየሚገኝ የኮቪድ 19 ታማሚ ወይም በኮቪድ-19 በሽታ ተይዟል ተብሎ የተጠረጠረ ሰውየሚከተሉትን ጥንቃቄዎችየማድረግ ግዴታ አለበት**

1) በቤተሰብ ወይም በራሱ ተለይቶበተዘጋጀበቂ የአየር ዝውውር ያለው (በርና መስኮት)ባለውክፍልውስጥመቆየት፣
2) ከሌላው የቤተሰብ አባላት በ 2 የአዋቂ ርምጃ ርቀት መጠበቅ እንዲሁም የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ መጠቀም፣
3) ራስንቢያንስለ 14 ተከታታይቀናት በመለየት መቆየት፣ በነዚህ ወቅቶች ከቤት አለመውጣት፣ ክትትል ከሚያደርጉ የጤና ባለሙያዎች ጋር ለሚኖር ግንኙነት መስመር ክፍት ማድርግ፣ ለዚህም መስማማቱን በተዘርጋውና በቀጣይ በሚዘረጉት የአሰራር መንገዶች ማረጋገጥ፣
4) የኮቪድ-19 በሽታ ምልክቶቹ ከተባባሱ ወዲያውኑ ለሚመለከተው ተቋም በስልክ ሪፖርት ማድረግ፣
5) አፍእናአፍንጫንበተገቢውመንገድ መሸፈን፣ የተጠቀሙበትን ሶፍት፣ የአፍእናአፍንጫመሸፈኛማስክ፣ የእጅ ጓንትና መሰል ቁሳቁሶችን ክዳን ባለው ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ወይም በፕላስቲክ ከረጢት ቋጥሮ በጥንቃቄ ማስወገድ፣

7. **A COVID-19 patient in home isolation and care or a person who is suspected to be infected with COVID-19 has a duty to take the following precautionary measures:-**

1) Staying in a well-ventilated room (with a door and window) separately dedicated by the family or the patient;
2) Maintaining a distance of two adult strides from the rest of the family and wearing mask;
3) Maintaining self-isolation for at least 14 consecutive days, staying at home during these days, availing communication lines for health care professionals responsible for following up, ensuring he agrees to this by using the procedure in place and those that will be implemented in the future.
4) Immediately report to the appropriate body via telephone if the COVID-19 symptoms get worse;
5) Wearing a mask properly; properly disposing used tissue papers, masks, gloves, and other waste generated by placing them in a waste bin with a lid after carefully putting them in plastic bags;

6) ማንኛውም ንክኪ በሚኖርበት ወቅት በውሃና ሳሙና መታጠብ ወይም በሳኒታይዘር የእጅን ንጽህና መጠበቅ፣
7) ሰዎችበጋራከሚጠቀሙባቸውእንደሳሎን፣ መታጠቢያ እና ምግብ ማብሰያ ያሉ በታዎች በተቻለ መጠን ከመጋራት መቆጠብ ወይም መቀነስ፣
8) የተለያዩየመጠቀሚያእቃዎችን፣ በሮችንእናየመሳሰሉትንነገሮችከመንካትመቆጠብ፣ እነዚህን እቃዎች ነክቶ ከሆነም ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት በአግባቡ እንዲጸዱ የማድረግ፣
9) ከተቻለ ሌሎች የማይጠቀሙባቸውን መጸዳጃ ቤቶች፣ ማእድ ቤቶችና ሌሎች መገልገያ እቃዎችን የመጠቀም፣ ካልሆነ ከተገለገሉ በኋላ በሳሙና እና በውሃ ማፅዳት።

6) If there is any contact with the patient, perform hand hygiene by washing hands with water and soap or using sanitizer;
7) To the extent possible, avoid or minimize time spent in shared spaces such as living rooms, kitchen and bathrooms;
8) Avoid toughing various utensils, doors, and other similar materials; if such items have been touched by the patient, properly wash before use;
9) If possible, use bathrooms, kitchens, and other utensils others do not use; if not, clean with water and soap after use.

## ክፍል አራት

## የኳራንቲን እና የድንበር ላይ ጤና ቁጥጥርን በተመለከተ

## Part Four

## Quarantine and Border Health Control

**8. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ አለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች በኩል የኮሮና ቫይረስ የRT PCR ምርመራ ውጤት ይዞ የሚመጣ መንገደኛን በተመለከተ**

1) ከትራንዚት መንገደኛ በስተቀር በአገሪቱ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ በኩል የሚገባ ከ አስር አመት ዕድሜ

**8. Traveler with a test result of RT PCR coming through international airports in Ethiopia**

1) Any international traveler above the age of ten , except transit passenger, coming through international airports of the country, shall bring a certificate of negative RT PCR test from the country he is

በላይ የሆነ ማንኛውም ተጓዥ ከመጣበት ሀገር ከ 120 ሰዓት ወይም አምስት ቀን በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ የRT PCR ምርመራ ኔጌቲቭ ውጤት ይዞ መምጣት አለበት። መንገደኛው በአየር መንገዱ የጤና ምርመራ ዴስክ የሙቀት እና የኮቪድ-19 ምልክቶች ልየታ ከተደረገ በኋላ አድራሻው ተመዝግቦ ለ7 ቀናት በቤቱ ራሱን ለይቶ የመቆየት ግዴታ አለበት፣

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (1) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የተረጋገጠ የRT PCR ምርመራ ኔጌቲቭ ውጤት ይዞ ያልመጣ ዲፕሎማት ለ14 ቀናት በቤቱ ራሱን ለይቶ የመቆየት ግዴታ አለበት፣

3) በአገሪቱ አለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል የሚገባ ማንኛውም ተጓዥ የኮቪድ-19 ምልክት የሚያሳይ ከሆነ መንግስት በለያቸው ጊዜያዊ ለይቶ ማቆያ እንዲገባ ተደርጎ በተቀመጠው የኮቪድ-19 የህክምና ማንዋል መሰረት ክትትል የሚፈጸም ይሆናል፣

4) የኮሮና ቫይረስ ፖዚቲቭ የሆነ ማንኛውም ሰው ወደ ሀገር ውስጥ መግባት የተከለከለ ነው።

coming from done up to 120 hours or five days before arriving in Ethiopia; after the traveler's temperature and any COVID-19 symptoms have been checked at airport's health control desk, his address shall be registered, and he has a duty to self-quarantine at home for seven days;

2) Without prejudice to sub-article (1) of this article, a diplomat with no certificate of negative RT PCR test has a duty to self-quarantine at home for 14 days;

3) If any traveler arriving at the Bole International Airport shows any symptom of COVID-19, he shall be taken to one of the temporary isolation centers prepared by the government where he will obtain follow up in accordance with the COVID-19 medical manual;

4) Any person who is corona virus positive is prohibited from entering the country.

**9. በአገሪቱ አለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች በኩል የኮሮና ቫይረስ የRT PCR ምርመራ ውጤት ሳይዝ የሚመጣ ከስደት ተመላሽ**

1) በአገሪቱ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ የሚገቡ ተመላሾች ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ከሚመጡበት ሀገር 120 ሰአት ወይም አምስት ቀን በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ የRT PCR ኔጋቲቭ ምርመራ ውጤት ይዘው እንዲመጡ ይደረጋል፣

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (1)እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 ንዑስ-አንቀጽ (3) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ወደ ሀገር የሚመጣ ከስደት ተመላሽ 120 ሰአት ወይም አምስት ቀን በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ የRT PCR ኔጋቲቭ ምርመራ ውጤት ይዞ ካልመጣ፣ ለRT PCR ምርመራ ናሙና ተወስዶለት አድራሻው ተመዝግቦ ውጤቱ እስኪመጣ ድረስ በቤቱ ራሱን ለይቶ የማቆየት ግዴታ አለበት

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (2) መሰረት የተደረገውምርመራ ውጤቱ ኔጋቲቭ ከሆነ አስፈላጊው ምክር ተሰጥቶት እስከ 7ኛው ቀን ድረስ በቤቱ ራሱን ለይቶ እንዲቆይ

**9. A returnee coming through international airports of the country with no certificate of negative RT PCR test**

1) In collaboration with the Ministry of Foreign Affairs, returnees coming through international airports of the country shall be made to bring a certificate of negative RT PCR test from the country they are coming from done up to 120 hours or 5 days before arrival;

2) Without prejudice to sub-article (1) of this article and Article 8(3) of this Directive, if a returnee does not bring a certificate of negative RT PCR test from the country they are coming from done up to 120 hours or 5 days before arrival, he has the duty to give sample of RT PCR test, have his address registered and self-quarantine at home until the result of the test is known;

3) If the result of the test done in accordance with sub-article 2 of this article is negative, the necessary advise shall be provided and the traveler will self-quarantine at home for 7 days; if the laboratory test

ይደረጋል፣ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤቱ ፖዚቲቭ ከሆነ በተቀመጠው የኮቪድ-19 የህክምና ማንዋል መሰረት ህክምና እና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል።

result is positive, he shall obtain medical care and follow up in accordance with the COVID-19 medical manual.

**10.በአገሪቱ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ በኩል የሚያልፍ የትራንዚት መንገደኛን በተመለከተ**

1) በአገሪቱ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ በኩል የሚገባ ማንኛውም የትራንዚት መንገደኛ አየር መንገዱን ለቆ ወደ ከተማ መግባት የለበትም

2) የኢትዮጵያ አየር መንገድና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የትራንዚት መንገደኛ አየር መንገዱን ለቆ ወደ ከተማ እንዳይገባ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፣

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (1) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ከ24 ሰዓት በላይ ትራንዚት ላላቸው መንገደኞች በረራቸው እስኪደርስ ድረስ አየር መንገዱ በለያቸው ሆቴሎች ተለይተው መቆየት ይችላሉ ። በነዚህ ወቅትም አየር መንገዱም ሆነ ሆቴሉ የትራንዚት መንገደኞቹ ወደ ህብረተሰቡ እንዳይቀላቀሉ ተገቢውን ቁጥጥር የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

**10. Transit passenger passing through international airports of the country**

1) Any transit passenger entering international airports of the country is not allowed to leave the airport and enter the city

2) Ethiopian Airlines and other concerned bodies have a duty to ensure the transit passenger does not leave the airport and enter the city;

3) Without prejudice to sub article 1 of this article, transit passengers with stop over for more than 24 are required to self-quarantine at the hotel designated by the air line. During such time, the airline and the hotel have the duty to ensure that the transit passenger do not mix with the general public.

## 11. በየብስ ድንበር የሚገቡ ሰዎችን በተመለከተ

1) በየብስ ድንበር በኩል የሚገባ ሰው 120 ሰአት ወይም አምስት ቀን በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ የRT PCR ኔጋቲቭ የምርመራ ሰርትፊኬት ይዞ የሚመጣ ከሆነ የሙቀት መለካትና የኮቪድ-19 ምልክቶች ልየታ ተደርጎለት ምንም ምልክቶችን ካላሳየ አድራሻው ተመዝግቦ ለ7 ቀናት በቤቱ ራሱን ለይቶ የመቆየት ግዴታ አለበት፣
2) በየብስ ድንበር በኩል የሚገባ ማንኛውም ሰው 120 ሰአት ወይም አምስት ቀን በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ የRT PCR ኔጌቲቭ የምርመራ ሰርትፊኬት ይዞ መምጣት የማይችል ከሆነ በመግቢያ ኬላ ላይ የሙቀት መለካትና የኮቪድ-19 ምልክቶች ልየታ ተደርጎለት ምንም ምልክት የማይታይበት ከሆነ አድራሻው ተመዝግቦ ለ14 ቀናት በቤቱ ራሱን ለይቶ የመቆየት ግዴታ አለበት። ነገር ግን በሙቀት መለካትና የኮቪድ-19 ምልክቶች ልየታ ጊዜ የኮቪድ በሽታ ምልክቶችን ያሳየ ሰው መንግስት ወደለየው የጊዜያዊ ለይቶ ማቆያ የመሄድ ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህም በየኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና

## 11. People crossing land borders

1) If a person entering the country through land border brings a certificate of negative RT PCR test done up to 120 hours or 5 days before arrival, after his temperature and COVID-19 symptoms are checked and his address is registered, he has a duty to self-quarantine at home for 7 days;
2) If a person entering the country through land border cannot bring a certificate of negative RT PCR test done up to 120 hours or 5 days before arrival, his temperature and COVID-19 symptoms shall be checked and if he shows no symptoms, he has a duty to self-quarantine at home for 14 days. However, after checking his temperature and symptoms of COVID-19, if the person shows symptoms of the disease, he has a duty to go to one of the temporary isolation centers prepared by the government where he will obtain follow up in accordance with the COVID-19 medical manual prepared by the Ethiopian Public Health Institute;

ኢንስቲትዩት በተዘጋጀው ፕሮቶኮል መሰረት ክትትል የሚደረግለት ይሆናል፣

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (2) መሰረት ወደ ለይቶ ማቆያ የገባ ሰው ናሙና ተወስዶ ከተቻለ የRT PCR ምርመራ ይደረግለታል፣ ይህ በማይቻልበት ጊዜ ወደፊት በምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን በተረጋገጠ ፈጣን የምርመራ ስልት (RDT) የሚደረግ የምርመራ ማረጋገጫ እንደአማራጭ ምርመራው እንዲከናወን ይደረጋል። በፈጣን የምርመራ ስልት (RDT) የሚደረጉ ምርመራዎች እና የምርመራ ውጤት ትርጉም እና ቀጣይ እርምጃዎች ለዚሁ ተብሎ በየኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በሚዘጋጅ ፕሮቶኮል የሚወሰን ይሆናል።

4) በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ቢኖሩም ድንበር አቋራጭ ተሽከርካሪዎችን የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎችና ረዳቶች እና የኢትዮ-ጂቡቲ የባቡር ትራንስፖርት አሽከርካሪዎችና ረዳቶች የትራንስፖርት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚገዙ ይሆናል።

3) If possible, a person who has been taken to an isolation center in accordance with sub-article 2 of this article will give sample for RT PCR testing. If this is not possible, Rapid Diagnostic Test (RDT) approved by the Ethiopian Food and Drug Administration will be used as an alternative testing mechanism. The details of testing done using Rapid Diagnostic Test (RDT), the implication of the test results, and proceeding measures will be determined by a protocol that shall be prepared for this purpose by the Ethiopian Public Health Institute.

4) Notwithstanding the provisions of this article, drivers of cross nationals vehicles and captains of train and their co-drivers and co-captains shall be governed by a directive issued by the Ministry of Transport.

**12. ከውጭ አገር የሚጓጓዝ አስክሬን**

1) ማንኛውም አስክሬን ከውጭ ሀገር ወደኢትዮጵያ በሚላክበት ጊዜየሞት ምክንያትን የሚገልጽ የሞት ሰርትፍኬት አብሮ መላክ አለበት፣
2) ማንኛውም ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ወደሀገር ውስጥ የሚገባ አስክሬን የቀብር አፈጻጸም ስርዓት በዚህ መመሪያ በክፍል አምስት በተዘረዘረው መሰረት የሚካሄድ ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## የቀብር ስነ ስርአት፣ የአስክሬንማጓጓዝ እና የሀዘን ስነ ስርአት

**13. በአስክሬን ማስተካከልና ግነዛ ወቅት ሊደረጉ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች፡-**

1) ሞት የተከሰተባቸው የጤና ማዕከላት ሟች በማዕከሉ ሲገለገልባቸው የነበሩ የግል ቁሳቁሶች በጸረ ተህዋሲያን ውህድ በማጽዳት ለቤተሰብ የማስረከብ እና ሌሎች በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ አለባቸው፣
2) የሟች ቤተሰብ ወይም ለሟች ኃላፊነት ያለበት ሰው አስክሬን ከጤና ተቋም ወይንም ከውጭ ሀገር በሚረከብበት ጊዜ የአስክሬን መለየት ሂደት ላይ

**12. Human remains transported from abroad**

1) Any corpse sent to Ethiopia from abroad must be accompanied by a death certificate indicating the cause of death;
2) The funeral ceremony of any corpse entering the country in the manner stated above shall be conducted in accordance with Part Five of this Directive.

## Part Five

## Funeral, Corpse Transporting and Consolation programs

**13. Precautions which need to be taken during corpse arrangement and enshrouding**

1) Health centers where the death occurred have a duty to clean with disinfectants the materials the deceased has been using, return the materials to the family, and perform activities provided in manual prepared at the national level.

2) The family of the deceased or any person responsible for collecting the corpse from the health center or abroad has a duty not to have any contact with the corpse or the coffin.

ከአስክሬኑም ሆነ ከሳጥኑ ጋር ማንኛውም አይነት ንክኪ ያለማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

3) ከጤና ተቋም ውጭ ሞት ሲከሰት በአስክሬን ማስተካከልም ሆነ ግነዛ ሂደት ከሟች ቤተሰቦችም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖሩ ማንኛውም ግንኙነቶች ወይም በቦታው የሚደረግ እንቅስቃሴ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀትን በጠበቀ መልኩ መሆን እና አስክሬን የሚያስተካክሉና የሚገንዙ ሰዎች የእጅ ጓንት፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፣ከፕላስቲክ የተሠራ ጋዋን ወይም ላስቲክ እንደ አስፈላጊነቱም የአይን መከላከያ ወይም መነጽር መልበስ አለባቸው፣

4) የሟች ቤተሰብ ወይም ለሟች ኃላፊነት ያለበት ሰው አስከሬኑንም ሆነ አስክሬንያለበትን ሳጥን ያለመነከካት ወይም ያለመሳም ፣ አስክሬን ያለበትን ሳጥን ወይም አስክሬን የተጫነበትን ሌላ እቃ፣ሟች በታመመበት ወቅት በቤት ውስጥ ተኝቶ የነበረበት አልጋ፣ ሲገለገልባቸው ወይም በዙሪያ የነበሩ እቃዎች፣ የቤቱን ወለልና ሌሎች ከሟች ጋር ንክኪ የነበራቸውን ቁሳቁሶች በጸረ ተህዋሲያን ውህድ እንዲፀዳ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

3) When a death occurs outside health centers, the arrangement of the corpse or any other movement in the enshrouding processes needs to be conducted maintaining a distance of two adult strides from the families of the deceased and other individuals; the individuals who arrange and enshroud the corpse shall wear a glove, face mask, a gown made of plastic or plastic and wear goggles or eyeglasses as necessary.

4) Families of the deceased or a person responsible for the deceased has a duty not to touch or kiss the corpse or the coffin; the person also has the duty to have the coffin or any other material used to move the corpse, the bed the deceased was sleeping on while he was sick, materials the deceased has been using, materials which were around the deceased, the floor of the house and any other material which had any contact with the deceased cleaned with disinfectants.

5) ከጤና ተቋም ውጭ ሞት ተከስቶ የሟችን አስክሬን የሚገንዙ ሰዎች የአስክሬን ማስተካከሉና መገነዝ ሂደቱ ካጠናቀቁ በኋላ የተጠቀሙበትን የእጅ ጓንት፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ እና ሰውነታቸውን የሸፈኑበትን ፕላስቲክ ወይም ጋዎን በአግባቡ የማስወገድ እና እጆቻቸውን በውሃ እና በሳሙና የመታጠብ ግዴታ አለባቸው፣

6) በለቅሶ በታ የተገኘ ማንኛውም ሰው ተገቢውን የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የማድረግ፣ እንዲሁም ሌሎች በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ማንዋል ላይ የተዘረዘሩትን በአስክሬን ግነዛ እና ማስተካከል ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የመተግበር ግዴታ አለበት።

## 14. በአስክሬን መጓጓዝ ወቅት እና በቀብር አፈፃጸም ወቅት የሚኖሩ ግዴታዎች

1) ከጤና ተቋም ውጭ ሞት ተከስቶ የሟች አስክሬን ከተገነዘ በኃላ የሟች ቤተሰብ ወይም ለሟች ሀላፊነት ያለበት ሰው በ24 ሰዓት ውስጥ እንዲቀበር ማድረግ ኃላፊነት አለበት

2) በጤና ተቋማት ላይ ሞት ከተከሰተ በኋላ ወይንም አስክሬን ከውጭ ሀገር የሚገባ ከሆነ የሟች ቤተሰቦች አስክሬን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ቤት

5) Individuals who enshroud the corpse when death occurs out of health centers, after finishing the enshrouding, have a duty to dispose of the used glove, face mask, the plastic used to cover their body or gown appropriately and wash their hands with soap and water.

6) Any person visiting for mourning/consolation shall wear a face mask and shall take all precautionary measures provided in the manual prepared at the national level for arranging corpse and enshrouding.

## 14. Duties imposed while transporting the corpse and funeral ceremony

1) Families of the deceased or the person responsible for the deceased, who passed away outside a health center, has a duty to arrange the burial within 24 hours after enshrouding.

2) Families of the deceased have a duty to take the corpse directly to burial after they receive the corpse either from a health center or abroad.

ሳይወስዱ በቀጥታ ወደ ቀብር ቦታ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፣

3) አስከሬኑን ወደ ማጓጓዣው የሚጭን ወይም ተሸክሞ ወደ ቀብር የሚወስድ ማናቸውም ሰው አፍና አፍንጫውን የመሸፈን እንዲሁም የእጅ ጓንት የማድረግ ግዴታ አለበት፣

4) የቀብር ስነስርዓት አፈጻጸም በአጠቃላይ ከ50 ሰውሳይበልጥ፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ በማድረግና ሁለት የአዋቂ እርምጃ በመራራቅ መከናወን አለበት፣

5) ማንኛውም በቀብሩ ላይ የተገኘ ሰው፣ በአስክሬን ማጓጓዝ ወይም በግብአተ መሬት ወቅት የተሳተፈ ሰው፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀው ማንዋል በሚያዘው መሰረት እጁን በውሃና ሳሙና የመታጠብ ወይም በሳኒታይዘር የማፅዳት እና ሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመተግበር ግዴታ አለበት።

3) Any person who transports or carries the corpse to burial has a duty to wear a face mask and gloves.

4) The funeral ceremony shall be held with people not more than 50, wearing a face mask and maintaining a distance of two adult strides.

5) Any person who attended the funeral participated in transporting the corpse or in burying the deceased has a duty to wash his hands with water and soap or clean with a sanitizer, and implement other precautionary measures.

## 15. ከቀብር ስነ-ስርአት በኋላ የሚኖሩ ግዴታዎች

1) ከቀብር በኋላ ለቅሶ መቀመጥ በድንኳን፣ በቤት ውስጥ ወይም ለዚሁ በተዘጋጀ ቦታ ላይ ሲደረግ ሀዘንተኛው እና የቤተሰቡ አባላት እና

## 15. Duties imposed after a funeral ceremony

1) After the burial, while sitting in a tent, in a house, or a place prepared for the ceremony, the mourners and members of the family shall not be more than 50 individuals, maintain a distance of two adult strides, avoid touching each

ለቅሶ የሚደርሰው ሰው ከ50 ሰው ሳይበልጥ እና ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀትን በመጠበቅና ባለመነካካት፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ በማድረግ እና ሌሎችበአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ማንዋል ላይ የተቀመጡትን ጥንቃቄ ተፈጻሚ በማድረግ መሆን አለበት፣

2) በለቅሶ እና በቀብር ስርአት በኋላ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመነካካት ወይም ሊያነካካ በሚችል መልኩ መመገብ፣ ወይም በሌሎች ሰዎች በተነካኩና ባልታጠቡ እቃዎች መመገብ የተከለከለ ነው፣
3) ማንኛውም ለቅሶ ሊደርስ የመጣ ሰው ወደ ለቅሶ ቤት ከመግባቱ በፊትና ከለቅሶ ቤት ሲወጣ እጁን በውሃና ሳሙና የመታጠብ ወይም በሳኒታይዘር የማፅዳት ግዴታ አለበት፣
4) ሌሎች ከሀይማኖታዊ ተቋማት ውጪ የሚከናወኑ የሀዘን ስርአቶች እንደ ሰባት፣ አርባ ፣ሙት አመትና ሰደቃ የመሳሰሉትን ለማክበር የሚኖሩ ማህበራዊ ስብስብን በተመለከተበዚህ መመሪያ አንቀጽ 22መሰረት ይፈጸማል።

other, wear a face mask and apply other precautionary measures provided in the manual nationally prepared.

2) During and after the funeral ceremony, it is prohibited to touch each other or eat in a way that will make individuals touch each other or eat with materials/utensils not washed after being used by other individuals.
3) Any individual who visits for mourning/consoling the family has a duty to wash his hands with water and soap or clean with a sanitizer before entering the house and while leaving.
4) Other gatherings held outside of religious institutions as part of mourning ceremonies such as sebat, arba, mut amet, and sedeqa shall be held in accordance with article 22 of this Directive.

**16.ሞት ሲከሰት የሚመለከታቸው አካላት ግዴታዎች**

1) እድሮች ወይም ሌሎች የሚመለከታቸው ማህበራዊ አደረጃጀቶች በአስክሬን አገናነዝ፣በጉዞ ወቅት እና በቀብር ስነስርዓቱ ላይ እንዲሁም በሀዘን ቤት በሚኖር የቆይታ ጊዜ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የኮቪድ መከላከል የጥንቃቄ መስፈርቶች መሟላታቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፣

2) በሥርዓተ ቀብር ላይ የሚገኙት የሀይማኖት ተቋማት ኃላፊዎች ወይም የሀይማኖት አባቶች አፍና አፍንጫቸውን የመሸፈን፣ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት የመጠበቅ፣ በስርዓቱ ላይ ከ50 ሰው በላይ አለመገኘቱን የማረጋገጥ፣ በለቅሶ ስርአቱ ላይ ለሚገኘው ማህበረሰብ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር የተያያዘ ትምህርት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፣

3) በፌዴራልና ክልሎች በየደረጃው የሚገኙ የጤና፣ የፖሊስ እና ሌሎች የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት፣ የዞን፣ የከተማ፣ የወረዳ እና የቀበሌ አስተዳደሮች በዚህ ክፍል ስር የተቀመጡትን ግዴታዎች

**16. Duties imposed on concerned bodies when death occurs**

1) While enshrouding, transporting the corpse, conducting funeral ceremonies, and while staying in a mourning house, Elders and other such social structures have a duty to ensure the implementation of precautionary measures provided in this Directive to prevent COVID 19.

2) Religious leaders and religious fathers have a duty to wear face masks, maintain a distance of two adult strides, ensure people attending the ceremony are not more than 50, and teach the attendees facts regarding the COVID-19 pandemic.

3) Health institutions, the police, and other concerned state institutions at the federal and regional level, zonal, city, woreda, and kebele administrations have a duty to ensure the fulfillment of obligations listed under this part and list of obligations assigned to them by

መሟላታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት እና በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ማንዋል መሰረት የተጣሉባቸውን ዝርዝር ግዴታዎች የመተግበር ግዴታዎች አለባቸው።

## ክፍል ስድስት

## በስብሰባ ወቅት መወሰድ ስላለባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

### 17.የተሰብሳቢዎች ብዛትን በተመለከተ

1) በዚህ ክፍል የተዘረዘሩትን እና ስብሰባን ማካሄድን በተመለከተ በተዘጋጀው ማንዋል ላይ የተካተቱትን የጥንቃቄ እርምጃዎች አሟልቶ እስከ50 ሰው ሆኖ መሰብሰብ ይቻላል፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ላይ የተቀመጠው እንዳለ ሆኖ ከ50 ሰው በላይ መሰብሰብ ግዴታ ሆኖ ከተገኘ ስብሰባው ሊደረግበት የታሰበበት አዳራሽን ጠቅላላ ስፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት በታው ሊይዝ ከሚችለው ሰው ብዛት አንድ አራተኛውን በማይበልጥ ሰው ለሰላም ሚኒስቴር እና በተዋረድ ባሉ የክልል፣ ዞን እና ወረዳ የሰላም እና ፀጥታ መዋቅሮች አስቀድሞ በማሳወቅ ሊከናወን ይችላል።

the manual prepared at the national level.

## Part Six

## Precautionary Measures that Shall Be Taken During Meetings

### 17. Concerning the number of attendees

1) It is allowed to have a meeting of up to 50 individuals by taking the precautionary measures listed in this part and precautionary measures provided in the manual prepared for organizing a meeting.
2) Without prejudice to sub-article (1) of this article, when a meeting demands the attendance of more than 50 individuals, it can be held with prior notification to the Ministry of Peace and other regional, zonal, and wereda hierarchical peace and security structures taking into account the area of the hall in which the meeting will be held, and it shall not be above one-fourth of the hall's total holding capacity.

## 18. ስብሰባውን የጠራው አካል መውሰድ ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃዎች

1) የግድ ካልሆነ በስተቀር በአካል የሚደረጉ ስብሰባዎችን ከማመቻቸት ይልቅ በተቻለ መጠን በኦንላይን አማራጮች ስብሰባዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፣
2) ስብሰባውን በሚጠራበት ጊዜ ስብሰባው በተሳታፊዎች መሀል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ያህል (2 ሜትር) ለመጠበቅ በሚያስችል አዳራሽ ከ50 ሰው ሳይበልጥ መካሄድ መቻሉን የማረጋገጥ፣ የእጅ መታጠቢያ ወይም ከአልኮል የተዘጋጀ የእጅ ማጽጃ (ሳኒታይዘር) በበቂ መዘጋጀቱን የማረጋገጥ እና ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ ሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመተግበር ግዴታ አለባቸው፣
3) ለስብሰባ የሚጠሯቸውን ተሳታፊዎች ስለኮሮና ቫይረስ በሽታ መተላለፊያ እና መከላከያ መንገዶች እንዲሁም በስብሰባ ወቅት ሊከተሏቸው ስለሚገቡ የጥንቃቄ እርምጃዎች በቂ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

## 18. Precautionary measures that shall be taken by the host organizing the meeting

1) As much as possible, hosting meeting using online options than physical meetings unless it is mandatory;
2) While calling for a meeting, making sure the meeting hall can host 50 attendees, maintaining a distance of two adult strides (two meters) between the attendees, ensuring sufficient hand wash or alcoholic hand sanitizer is provided and implementing the precautionary measures provided in the manual prepared for such meetings.
3) Providing sufficient information about the coronavirus pandemic regarding ways of transmission and preventing the coronavirus, and inform the attendees of the rules on precautionary measures the attendees need to follow during the meeting.

**19.ስብሰባውን የሚያስተናግደው መስተንግዶ ሰጪ አካል መውሰድ ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃዎች**

1) የስብሰባ አዳራሾች በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖራቸው የማድረግ፣ የእጅ ንጽህናን ለመጠበቅ የሚያስችሉ በቂ ግብዓቶችን የማዘጋጀት፣ በተቻለ መጠን የተሰብሳቢዎች መግቢያና መውጫ የተለያየ እንዲሆን የማድረግ፣ ተሰብሳቢዎች የሚጠቀሙባቸው እና በተደጋጋሚ የሚነኩ ቁሳቁሶችን ቢያንስ በቀን ሁለት ጊዜ ጸረ ተህዋሲያን ውህድ የማፅዳት፣ እና ሌሎች በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመተግበር ግዴታ አለባቸው፣
2) የእያንዳንዱን ተሳታፊ ስም፣ስልክ እና አድራሻን መዝግቦ እስከ 14 ቀን ድረስ በፋይል የማቆየት እና በ14 ቀን ውስጥ በበሽታው የተያዘ ወይንም የተጠረጠረ ሰው ከሌለ መረጃውን የተሳታፊዎችን የግል መረጃ ሚስጥራዊነት በጠበቀ መልኩ የማስወገድ፣
3) ስብሰባው በተሳታፊዎች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ያህል (2 ሜትር) ተጠብቆ ከ50 ሰው ሳይበልጥ ስብሰባ የማካሄድ፣ እያንዳንዱ ተሰብሳቢ የአፍና

**19. Precautionary measures that need to be taken by the person providing conference services during the meeting**

1) Making sure the meeting hall to has sufficient air ventilation, preparing sufficient materials useful for keeping hand hygiene, as much as possible separating the entrance and the exit, cleaning materials the participants use and repeatedly touch with disinfectant at least twice a day, and taking other precautionary measures provided in the manual.
2) Registering and keeping the name, phone number, and address of each participant for 14 days and if no one is infected or suspected of being infected with the pandemic, disposing of the record in a way that protects the privacy of the personal information of the participants.
3) Making sure the meeting with not more than 50 participants is held, maintaining a distance of two adult strides (two-meters), prohibiting a participant without a face mask from entering the meeting hall, and

አፍንጫ መሸፈኛ ካላደረገ ስብሰባ ወደሚደረግበት በታ እንዳይገባ የመከልከል፣ እንዲሁም ከመግባቱ በፊት የሙቀት ልኬት የማድረግ ግዴታ አለበት፣

measuring the temperature of each participant before entering the hall.

4) በስብሰባው ወቅት የኮቪድ-19 የጥንቃቄ እርምጃዎችን አወሳሰድ በተመለከተ የሚከታተል፣ የሚቆጣጠርና አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስድ አንድ ሰው በቋሚነት የመመደብ፣

4) Assigning a person to follow, control, and take necessary COVID 19 precautionary measures during the meeting.

5) የኮቪድ ምልክት የታየበት ግለሰብ ቢኖር ለጤና ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ በአቅራቢያው ለሚገኙ የጤና ተቋም ወይም ባለሞያ የማሳወቅ ግዴታ እናበጊዜያዊነት ለማቆያ አገልግሎት የሚውል ለይቶ ማቆያ ክፍል ማዘጋጀት፣

5) Informing the ministry of health, the Ethiopian Public Health Institute, a nearby health institution, or health professional if any person shows symptoms of COVID-19; preparing a room which can be used as a temporary isolation room;

6) ተሰብሳቢዎች በእረፍት ሰአት ወይም በምሳ ሰአት አካላዊ ርቀታቸዉን እንዲጠብቁ የሚያስችል ምልክት የማስቀመጥእንዲሁም ሌሎች ከምግብ መስተንግዶ ጋር የተያያዙ አገልግሎች በሚሰጡበት ወቅት በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሙሉ በሙሉ የመተግበር ግዴታ አለባቸው።

6) Putting a mark for attendees during break time or lunchtime so that they can keep their physical distance and implement all the precautionary measures provided in the manual prepared regarding services related to serving food.

## 20. የስብሰባ ታዳሚ መውሰድ ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃዎች

1) የኮቪድ-19 ምልክቶች ካሳየ ማለትም የሳል፣ የሙቀት መጨመር ለመተንፈስ መቸገር ወይም ለኮቪድ 19 አጋላጭ ሁኔታ ውስጥ ከነበረ በበሽታው አለመያዙ እስካልተረጋገጠ ድረስ በስብሰባው አለመሳተፍ፣
2) ስብሰባው እስከሚጠናቀቅ ድረስ እንደምግብ ለመመገብ አይነት አስገዳጅ ተግባራት ውጭ በማንኛውም ጊዜ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል በአግባቡ የማድረግ፣ በስብሰባ ወቅት ጥያቄ በሚጠየቅበት እና ሃሳብ በሚሰጥበት ወቅት የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብሉን አለማውለቅ ወይም ወደአገጭ ዝቅ ያለማድረግ ግዴታ አለበት፣
3) ከማንኛውም ሰው ቢያንስ በሁለት ሜትር አካላዊ ርቀትን ጠብቆ መሳተፍ፣እጅን ቶሎ ቶሎ መታጠብ ወይንም በሳኒታይዘር ማፅዳት፣ የተጠቀሙበትን ሶፍት እና ሌሎች የተጸዳዱበትን ቁሶች በአግባቡ ክዳን ባለዉ ቆሻሻ ማስወገጃ ማስወገድ፣ ስብሰባው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚታደረው በዚያው በስብሰባው ቦታ ከሆነ በተቻለ መጠን በክፍል ውስጥ መቆየት እና ሌሎች በተዘጋጀው

## 20. Precautionary measures that need to be taken by attendees

1) Not participating in the meeting if he has COVID-19 symptoms such as coughing, fever, breathing difficulties, or was in a situation making him vulnerable to COVID-19 unless proved free from the pandemic.
2) Putting a face mask properly until the end of the meeting except for obligatory actions such as eating, not taking off the mask, or putting it on the chin while asking a question and forwarding an idea during the meeting.
3) Participating while maintaining a two-meters distance from every individual, washing or cleaning hands with sanitizer repeatedly, properly disposing of used soft papers and other disposable materials into a waste bin with a lid; after the end the meeting, if the participants are spending the night in the same place, as much as possible staying in their rooms and implementing all the precautionary measures provided in the manual.

ማንዋል የተዘረዘሩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሙሉ በሙሉ የመተግበር ግዴታ አለባቸው።

## ክፍል ሰባት

## በሀይማኖታዊ ስነስርዓት፣ በየቤት ውስጥ ማህበራዊ ዝግጅቶች፣ እና የአደባባይ በዓላት አከባበርወቅት ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

### 21.የሃይማኖት ስነስርዓቶችን አተገባበርን በተመለከት

1) ማንኛውም ሀይማኖታዊ ስርዓት የሚፈጽሙ ሰዎች ሀይማኖታዊ ስርዓቱን በሚፈጽሙበት ወቅት ከሁለት የአዋቂ እርምጃዎች በታች ተጠጋግቶ ስርዓቱን መፈጸም የተከለከለ ነው፣
2) የሀይማኖቱ ስርዓት የሚከናወንበት ህንፃ ውስጥ ህንፃው የሚሸፍነውን ጠቅላላ ቦታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቦታው ሊይዝ ከሚችለው ሰው ብዛት አንድ አራተኛውን የማይበልጥ ሰው በመያዝ ስርዓቱን ማካሄድ ይኖርባቸዋል፣
3) በእምነት ተቋማት ቅጥር ግቢ ውስጥ የእምነቱ ተከታዮች የእምነት ስርዓቱን በሚፈስጽሙበት ወቅት ሲቆሙም ሆነ

## Part Seven

## Cautionary Measures During Religious Ceremony, In-house Social Ceremonies, and Holidays Held on Public Squares

### 21. Conduct of Religious Ceremonies

1) It is prohibited for people responsible for performing any religious rituals to conduct the ceremony without ensuring that participants maintained a distance of two adult strides.
2) People responsible for performing the conduct of any religious rituals shall be responsible for ensuring that no more than one-fourth of the maximum occupancy number is held, which shall take into account the total area in the building where the religious ceremony is held.
3) The attending followers of the religious ceremony who may be standing or sitting next to one another in the premise of the religious

ሲቀመጡ የሁለት ሜትር ርቀት የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፣

institution shall maintain a two-meter physical distance.

4) ማንኛውም ሰው የአፍእና አፍንጫ መሸፈኛ ሳይደረግ ወደእምነት ተቋማት ቅጥር ግቢ ውስጥ መግባት የተከለከለ ነው፣

4) It is prohibited to enter into the premise of any religious institution without wearing a face mask.

5) ማንኛውም የእምነት ተቋም ስለበሽታው አስፈላጊውን መረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማድረስ፣ እንዲሁም የለሀይማኖቱ መሪዎች እና በእምነት ተቋሙ ውስጥ ለሚያገለግሉት የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፣

5) Every religious institution shall have the duty to deliver COVID-19 related essential health education through different means, and shall provide personal protective equipment to religious leaders and other individuals who serve in the religious institution to control the transmission of the diseases.

6) ማንኛውም ሰው የእምነት ተቋማት የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመከላከል የሚያወጧቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የመፈጸም ግዴታ አለበት፣

6) Every individual shall comply with any COVID-19 preventive and control measures adopted by any religious institution.

7) ማንኛውም የእምነት ተቋም የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመከላከል የሚያወጣቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች በእምነቱ ተከታዮች መፈጸማቸውን የመቆጣጠር ግዴታ አለበት።

7) It shall be the duty of every religious institution to ensure implementation of and compliance with their COVID-19 prevention measures by followers of the respective religion.

## 22.የቤት ውስጥ ማህበራዊ ዝግጅቶችን በተመለከተ

1) ለልደት፣ ምረቃ፣ማህበር፣ሀዘንን መሰረት የሚያደርጉ ዝግጅቶች (ከቀብር እና ከቀብር መልስ ያሉ ስነስርዓቶች ውጭ) እና መሰል በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ ማህበራዊ በዓላት ከቤተሰብ አባላት ከሆኑ ውጭ ተጠራርቶ ማክበር የተከለከለ ነው፣
2) ከላይ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ማንኛውም ሰው ከ50 በላይ የማይበልጡ ሰዎች በመሆን እና ሁለት የአዋቂ እርምጃ (ሁለት ሜትር) ተራርቆ፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ በማድረግ እና ተገቢውን የኮቪድ 19 መከላከያ የንጽህና እርምጃዎች በመተግበር የሰርግ ስነስርዓት ማካሄድ ይችላል፣

## 23.የአደባባይ በዓላት አከባበርን በተመለከተ

1) ህዝብን በብዛት የሚያሳትፉ የአደባባይ ላይ በዓላት የወረርሽኑ ስርጭት መረጋጋት እስኪጀምር ድረስ በታቻለ አቅም ባይደረጉ ይመከራል፣

## 22. In-house social ceremonies

1) It shall be prohibited to conduct in-house ceremonies like birthday, graduation, mahber, and ceremonies related to mourning (except burial and ceremonies held immediately after burial), and holiday-related in-house social events with individuals other than family members.
2) Notwithstanding Sub-article (1) of this Article, it shall be allowed to hold a wedding ceremony for no more than 50 individuals provided that two adult strides (two-meter) distance is mainlined, participants wear face-mask, and the appropriate COVID-19 control and hygiene practice is implemented.

## 23. Holiday Held on Public Squares

1) It is recommended, as much as possible, not to hold holidays in a public square involving too many people until the prevalence of the pandemic is stabilized.

2) ማንኛውም በአደባባዮች ላይ የሚከበሩ በዓላትን የሚታደምም ሆነ አከባበሩን የሚያስተባበር ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ የማድረግ እና በአከባበርም ወቅት ሁለት ሜትር ርቀትን ጠብቆ የመቆምና መቀመጥ ግዴታ አለበት፣

3) ማንኛዉም በአደባባይ የሚከበሩ በዓላትን የሚያስተባብር አካል በዓላት የሚከበሩባቸው አደባባዮች የሚሸፍኑትን ጠቅላላ ቦታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቦታው ሊይዝ ከሚችለው ሰው ብዛት አንድ አራተኛውን የማይበልጥ ሰው በመያዝ ስርዓቱን ማካሄድ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፣

4) የበዓላቱ አስተባባሪዎች ወደ በዓላቱ የሚከበሩበት አደባባዮች የሚወስዱ መንገዶችን እና መግቢያ ቦታዎች ላይ የበዓላቱ ታዳሚዎች ተገቢውን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከላከያ መሟላታቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፣

5) የበዓላቱ አስተባባሪዎች አስፈላጊውን መረጃ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማድረስግዴታ አለባቸው፣

6) የበዓላቱ አስተባባሪዎች በአደባባይ ላይ የሚከበሩ በዓላት ወቅት መጨናነቅ እንዳኖር የመግቢያ እና የመውጫያ መንገዶችን መለየትን ጨምሮ ሌሎች

2) Every individual who attends or coordinates the conduct of any holidays in public square shall wear a face mask and maintain a two-meter distance while standing and sitting within the ceremony area.

3) Every individual who is responsible to coordinates the conduct of any holiday in a public square shall be responsible for ensuring that the event is conducted with no more than one-fourth of the maximum occupancy size, which shall take into account the total area covered by the location designed for the respective out-door event.

4) Coordinators of the holidays held in Public Square shall have the duty to ensure implementation of COVID-19 prevention measures by all individuals attending the ceremony at all major roads leading to and the entrance of the public square.

5) Coordinators of the holidays shall have the duty to deliver COVID-19 related essential health education through different means.

6) Coordinators of the holidays shall have the duty to designate separate entry and exit roads and take related measures to reduce crowding.

የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፣

7) የበዓላቱ አዘጋጆች እና አስተባባሪዎች በበዓሉ አከባበር ወቅት ሊደረጉ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች አስቀድሞ የመለየት፣ ለተሳታፊዎች የማሳወቅ፣ እና አፈጻጸሙን የመከታተል ግዴታ አለባቸው፣

8) ማንኛውም የአደባባይ በዓል ታዳሚ የበዓላቱ አዘጋጆች እና አስተባባሪዎች የሚያውጧቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የመተግበር ግዴታ አለባቸው፣

9) በበዓላት አከባበር ወቅት ማናቸውም ለንክኪ የሚዳርጉ እንቅስቃሴዎች እና የአከባበር ስርዓቶች የተከለከሉ ናቸው፣

10) እነዚህ ዝግጅቶች ወረርሽኙን ባገናዘበ መልኩ መከናወን መቻላቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ የመስጠት እና በአከባበር ወቅትም ደግሞ የጥንቃቄ እርምጃዎች የማይተገበሩ ከሆነ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አግባብ ባላቸው የመንግስት አካላት የሚፈጸም ይሆናል፣

11) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የአደባባይ በዓላት ማለት ህዝብን በብዛት የሚያሳትፉ በክፍት ስፍራዎች የሚደረጉ ስብስቦች ናቸው።

7) Hosts and coordinators of the holidays shall proactively identify preventive measures that must be exercised during the conduct of the ceremony, publicize the preventive measures to ceremony participants, and monitor its implementation.

8) Every individual shall comply with any COVID-19 preventive and control measures adopted by the hosts and coordinators of the holiday.

9) Any activity or ceremony procedure during the conduct of the ceremony that would cause contact shall be prohibited.

10) The relevant government organs shall be responsible for granting a permit for the conduct of such ceremonies after examining ceremonies are prepared with consideration of the pandemic, as well as to take the necessary measures during non-compliance with applicable measures.

11) For the purpose of this article, “public square holiday” mean holidays involving the public in mass and conducted in open public space.

## ክፍል ስምንት

## የመዝናኛ፣ የመስተንግዶ አገልግሎቶች እና ስፖርታዊ ውድድሮች ሊከተሉት የሚገቡ የጥንቃቄ እርምጃዎች

**24. አገልግሎት የሚሰጡ እንደ ካፌዎች፣ ባርና ሬስቶራንቶች፣መጠጥ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣የጭፈራ ቤቶች፣ እና የመዝናኛ እና መጫዎቻ አገልግሎት የሚሰጡ ስፍራዎች**

1) በአንድ ጠረጴዛ ከሰስት ሰው በላይ ማስተናገድ የተከለከለ ሲሆን በእያንዳንዱ ጠረጴዛ መካከል የሁለት ሜትር ርቀት ሊጠበቅ ይገባል፣
2) አገልግሎትን የሚሰጡ ሰዎች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛን የማድረግ ግዴታ አለባቸው፣
3) የሚስተናገዱ ሰዎች ከሚመገቡበት እና ከሚጠጡበት ወቅት ውጭ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛን የማድረግ ግዴታ አለባቸው፣
4) ተቋማቱ በመግቢያና መውጫ በሮች እና ሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች ላይ በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን ማዘጋጀት፣ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር የማድረግ፣ እንዲሁም ለሰራተኞቻቸው የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ

## Part Eight

## Cautionary Measures To Be Complied with By Recreations, Hospitality Services, and Sport Tournaments

**24. Hospitalities like cafes, bars, restaurants, night clubs, coffee shops, and recreational and amusement service providers**

1) It is prohibited to serve more than three people in a table, and there shall be a two-meter distance between each table.
2) Service providing individuals shall wear a face mask.
3) Customers shall wear a face mask except when eating and drinking.
4) Service providing facilities shall take necessary measures to control the pandemic by preparing required tools on the entrance and exit doors and other areas, ensure that rooms have adequate air ventilation, and provide employees with necessary personal protective equipment.

ቁሳቁሶችን የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፣

5) ተቋማቱ ተገልጋዮቻቸው የሚጠቀሙባቸው ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ የመጫዎቻ እቃዎች እና ሌሎች መሰል ቁሳቁሶችን ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኃላ በጸረ ተህዋሲያን ውህድ ማጽዳት ኃላፊነት አለባቸው፣

6) የሳውና እና መሰል አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማት በአንድ የአገልግሎት መስጫ ክፍል ውስጥ ከአንድ ሰው በላይ ወይንም ከአንድ ቤተሰብ አባላት ውጭ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፣

7) የጭፈራ ቤቶች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት አገልግሎት የሚሰጡበት ስፍራ ስፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት በታው ሊይዝ ከሚችለው ሰው ብዛት አንድ አራተኛውን የሚበልጥ ሰው ሳይዙ፣ በተገልጋዮች መሀል ሁለት የአዋቂ እርምጃ (ሁለት ሜትር) በሁሉም ጊዜ በማስጠበቅ፣ ማንኛውም ለንክኪ የሚዳርጉ እንቅስቃሴዎችን በመከልከል፣ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሙሉ በሙሉ በመተግበር ሊሆን ይገባል፣

5) Service providing facilities shall disinfect chairs, tables, game toys, and other related tools used by customers after every service session.

6) Facilities providing sauna and related kinds of services shall not allow more than one person or any person who is not a member of a family in one room.

7) Night clubs shall be responsible for ensuring that no more than one-fourth of the maximum occupancy size is occupied, which shall take into account the total area covered of the service provision area, the two-meter distance between customers is maintained, and prohibiting any activity that would create contact, and fully implementing other necessary measures.

8) ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሊወሰዱ የሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች በማንዋል በዝርዝር የሚቀመጡ ሲሆን ተቋማቱም ሆኑ ተገልጋዮች እነዚህን እርምጃዎች ሙሉ በሙሉ የመተግበር ግዴታ አለባቸው።

8) Besides the cautions provided above, additional cautionary measures shall be provided in a manual, and the institutions and customers shall fully comply with it.

**25.ሲኒማ ቤቶች፣ ቲያትር ቤቶች እና የስዕል ጋለሪ**

1) ተቋማቱ አገልግሎት የሚሰጡባቸውን በታዎች ከእያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍለ ጊዜ በኋላ በታዎቹን በጸረ-ተህዋሲያን ውህድየማጽዳት፣ ተገልጋዮች እጃቸውን እንዲታጠቡ በቂ ውሃና ሳሙና ወይም ሳኒታይዘር የማቅረብ፣ እና በመመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎች አክብሮ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፣

2) ተቋማቱ በመግቢያ እና መውጫ በሮችና ሌሎች አስፈላጊ በታዎች በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን ማዘጋጀት እንዲሁም ለሰራተኞቻቸው የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚረዱ የጥንቃቄ ቁሳቁሶችን የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፣

**25. Cinemas, theaters, and art galleries**

1) The institutions shall clean the service area with disinfectant after every session, provide enough water and soap or sanitizer for hand cleaning by customs, and provide service as per other applicable cautionary measures as defined under a directive.

2) Service providing facilities shall take necessary measures to control the pandemic by preparing required tools on the entrance and exit doors and other areas, ensure that rooms have adequate air ventilation, and provide employees with necessary personal protective equipment.

3) አገልግሎቱ የሚሰጥበት አዳራሽ ወይም ስፍራ ስፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት ቦታው ሊይዝ ከሚችለው ሰው ብዛት አንድ አራተኛውን የማይበልጥ ሰው በመያዝ እና ሁለት የአዋቂ እርምጃ (ሁለት ሜትር) በማራራቅ አገልግሎቱን መስጠት ይኖርባቸዋል፣

4) ተቋማቶቹ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ተገቢውን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከላከያ መሟላታቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፣

5) ማንኛውም ሰው በእነዚህ ተቋማት ለመስተናገድ ተቋማቶቹ የሚያውጧቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች የመተግበር ግዴታ አለበት፣

6) ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሊወሰዱ የሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች በማንዋል በዝርዝር የሚቀመጡ ሲሆን ተቋማቱም ሆኑ ተገልጋዮች እነዚህን እርምጃዎች ሙሉ በሙሉ የመተግበር ግዴታ አለባቸው።

3) Service providing facilities shall be responsible for ensuring that no more than one-fourth of the maximum occupancy size is occupied, which shall take into account the total area covered by the service providing hall and area, and two-meter distance between customers is maintained.

4) The institutions shall ensure compliance of necessary COVID 19 pandemic protections by their customers.

5) Every individual shall implement cautionary measures adopted by the service delivery institutions.

6) Besides the cautions provided above, additional cautionary measures shall be provided in a manual, and the institutions and customers shall fully comply with it.

## 26.ስፖርታዊ ውድድሮች

1) የወረርሽኙ ስርጭት ያለበት ሁኔታ በየጊዜው እይታየ በሌላ መመሪያ እስኪወሰን ድረስ የእግር ኳስ፣ መረብ ኳስ፣ የእጅ ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ ቴኒስ፣ አትሌቲክስ እና ሌሎች የስፖርት ውድድሮች በውድድሩ ላይ በቀጥታ የሚሳተፉ እና ለነዚሁ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ከሆኑት ውጭ ታዳሚዎች በሌሉበት መከናወን አለባቸው፣
2) የስፖርታዊ ውድድር አዘጋጆችም ሆኑ ተሳታፊዎችበዚህ ዙሪያ በሚወጡ ማንዋሎች የሚወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሙሉ በሙሉ በመተግበር ውድድሮችን ማካሄድ ይገባቸዋል፣
3) እነዚህ ውድድሮች ወረርሽኙን ባገናዘበ መልኩ መከናወን መቻላቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ የመስጠት እና በውድድር ወቅቶችም የጥንቃቄ እርምጃዎች የማይተገበሩ ከሆነ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አግባብ ባላቸው የመንግስት አካላት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 26. Sport tournaments

1) Until determined by another directive after considering the status of the pandemic prevalence, football, volleyball, handball, basketball, tennis, athletics, and other tournaments shall only be attended by people who directly participate in the tournament and other support staffs, and may not be attended by spectators and fans.
2) Hosts and participants of any sports tournaments shall conduct the tournament by fully implementing applicable cautionary measures to be adopted in a manual.
3) The relevant government organs shall be responsible for granting a permit for the conduct of such tournaments with consideration of the pandemic, as well as to take the necessary measures during non-compliance with applicable measures.

## ክፍል ዘጠኝ

## በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚገኙባቸው ተቋማት ላይ የተጣሉ ክልከላዎች እና መደረግ ያለባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

### 27.ክልከላዎች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች

1) የወረርሽኙ ስርጭት ያለበት ሁኔታ በየጊዜው እየታየ በሌላ መመሪያ እስኪወሰን ድረስ የአረጋዊያን መጦሪያዎች ስፍራዎች እና የማገገሚያ ማዕከላት ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን በአካል መጠየቅ የተከለከለ ነው

2) በማረሚያ ቤቶች ላይ የሚደረግ የታራሚን በአካል የመጎብኘት ሂደት በታራሚው እና በጠያቂው መሀል ሁለት የአዋቂ እርምጃ አካላዊ ርቀትን በመጠበቅ፣ ታራሚውም ሆነ ጠያቂው የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ በማስደረግ፣ ጠያቂው ወደማረሚያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ከመግባቱም በፊት እና ሲወጣ እጁን በውሃ እና ሳሙና እንዲታጠብ ወይንም በሳኒታይዘር እንዲያጸዳ በማድረግ፣ እንዲሁም ሌሎች በዝርዝር በማንዋል የሚወጡ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ተከትሎ መሆን አለበት፣

3) እነዚህ ተቋማት ላይ ሊተገበሩ ስለሚገቡ የጥንቃቄ እርምጃዎች

## Part Nine

## Restrictions and Cautionary Measures to be Applicable by Institutions for High-Risk Section of the Society

### 27. Restrictions and cautionary measures

1) Until determined by another directive after considering the status of the pandemic prevalence, it shall be prohibited to physically visit Elders care centers, and Rehabilitation centers.

2) Any physical visit of prisoners may only be conducted by requiring the prisoner and the visitor to keep a two-meter distance between, wearing a face mask, and requiring visitors to wash their hands or clean by sanitizer before entering and leaving the prison premise, as well as comply with other cautionary measures provided in implementing manuals.

3) Implementation of cautionary measures to be applied by such

የሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ሊተዳደሩ ይገባል።

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 28.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰውእና ተቋም ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት።

### 29.መመርያዎችና አሰራሮች

በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የዘርፍ መስርያ ቤቶች በየመስካቸው የሚያጣቸው መመርያዎችና አሰራሮች የኮቪድ 19 በሽታን ለመግታት ወይም ለመቀነስ በዚህ መመርያ ውስጥ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች የማይቃረኑና ተጣጥመው የወጡ መሆን አለባቸው።

### 30.የህግ ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተደነገጉ ክልከላዎችን እና ግዴታዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው በወንጀል ህግ አንቀጽ መሰረት የሚቀጣ ይሆናል።

### 31.መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ25/01/2013 ጀምሮ የጸና ይሆናል፤

**አዲስ አበባ መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም**

**ኤባ አባተ (ዶ/ር)**

**ዋና ዳይሬክተር**

**የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት**

institutions shall be in accordance with applicable directives.

## Part Ten

## Miscellaneous Provisions

### 28. Duty to cooperate

Every person and institutions shall have the duty to cooperate for the implementation of this Directive

### 29. Directives and Practices

Directives and practices adopted by any sectoral government office in the country shall not contradict and be in line with provisions of this Directive issued to control and mitigate transmission of the COVID-19 pandemic.

### 30. Legal liability

Any person who contravenes the restrictions and duties provided in this Directive shall be held accountable as per the relevant provisions of the Criminal Code.

### 31. Effectiveness of the Directive

This directive shall come in to effect on 05/10/2020.

**Addis Ababa October 05/ 2020**

**Ebba Abate (PhD)**

**Director-General**

**Ethiopian Public Health Institute**